# ገቢዎቻችን ህልውናችን

የገቢዎች ሚኒስቴር Ministry of Revenues

15ኛ ዓመት | ቁጥር 171 | መጋቢት 2016 ዓ.ም | በነፃ የሚታደል



በውስጥ ገፆቻችን



«ግብርን በወቅቱ አሳውቆ መክፈል ከአሳስፈላጊ የክርክር ሒደት ያድናል»

ገጽ 3



የጤፍ እንጀራ

ገጽ 5


ገቢዎችን የተመለከቱ ወቅታዊ፣ ትኩስ እና የተሟሉ መረጃዎችን ለማግኘት፡- በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎቻችን ይጎብኙ

1. በድረ ገጽ፡- www.mor.gov.e
2. በቴሌግራም፡- https://t.me/MoREthiopiaOfficial/169
3. በፌስቡክ፡- https://www.facebook.com/ERCA.info or ministryofrevenuesofethiopia /የገቢዎች ሚኒስቴር/
4. በዩትዩብ፡- https://www.youtube.com/@ministryofrevenuesofethiop1677/videos Or ministryofrevenuesofethiopia
5. በቲክቶክ አጫጭር መረጃ https://vm.tiktok.com/ZM61hdty2/

በቴሌቪዥን ፕሮግራሞቻችን

6. ዋልታ ቴሌቪዥን ሰኞ ማታ ከ 2፡30 ጀምሮ
7. ፋና ቴሌቪዥን ሐሙስ ማታ ከ2፡00 ዜና በኃላ
8. ኢቲዮጵያ ቴሌቪዥን /ኢ.ቢ.ሲ/ ቅዳሜ ማታ ከ2፡00 ዜና በኋላ

በሬድዮ ፕሮግራሞቻችን

9. ፋና ኤፍ ኤም ሬድዮ 98.1 ሐሙስ ማታ ከ2፡30 ጀምሮ
10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬድዮ 93.1 ማክሰኞ ጠዋት ከ2፡30 ጀምሮ
11. በወርሃዊ ጋዜጣችን፡- ገቢያችን ህልውናችን

# ሀብታሞች እንዴት ሀብታም ይሆናሉ?

በሰሎሞን ወርቁ



ቢሊየነሩ ቢልጌትስ

በፕላኔታችን ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብትን በመቆጣጠር ሀብታሞች እየበለጸጉ መሆናቸውን ሁላችንም እናውቃለን፡፡ አክስፋም በቅርቡ ባወጣው የአለም አቀፍ የሀብት አለመመጣጠን ሪፖርት መሰረት ከ2020 ጀምሮ ሀብታሞች አንድ በመቶ የሚሆነውን ከጠቅላላው አዲስ ሀብት ሁለት ሦስተኛውን የያዙ ሲሆን ይህም ዝቅተኛውን 99 በመቶ የሰው ልጅ በእጥፍ ይበልጣል፡፡


ወደ ገጽ 6 ዞሯል




ቢሊየነሯ ማክኬንዚ

# የወጪ መጋራት አከፋፈል



በሺመልስ ሲሳይ

የወጪ መጋራት ክፍያ በደንብ ቁጥር 154/2000 እና በመመሪያ ቁጥር 71/2004 የወጣ ሲሆን ዓላማውም በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመደበኛው መርሐ-ግብር የተመረቁ ተማሪዎች መንግሥት ለትምህርት ያወጣውን ወጪ እንዲጋሩ ለማድረግ ነው፡፡ በዚህ ሥርዓትም መንግሥት ለትምህርት ያወጣው 15 በመቶ እንዲሁም ለምግብና ለመኝታ የወጣው ወጪ ሙሉ በሙሉ በተመራቂዎቹ ይሸፈናል፡፡

መመሪያ የሚመለከታቸውም ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ወደ መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብተው በመደበኛው መርሃ ግብር የተመረቁትን ነው፡፡ የክፍያ


ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀጽ


**ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**

የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ አካሉ ጴጥሮስ ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
ሰሎሞን ወርቁ

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፊር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 11-6-17-84-90 ኮድ 8490 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት፡- www.mor.gov.et ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia

**ስታክስ እና ስጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ፡- 8199**




# መልካም ስምን እና ገጽታን ለመጠበቅ

ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድትታወቅ ካደረጓት መገለጫዎች አንዱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው። አየር መንገዱ ሊታወቅ የቻለው በዘመናዊ አውሮፕላኖቹ፣ በአውሮፕላን አብራሪዎቹ፣ በቴክኒሻኖቹ፣ በበረራ አስተናጋጆቹ ደረጃውን የጠበቀ መስተንግዶ እና በሌሎችም ምክንያት ናቸው።

በአውሮፕላን ጣቢያው የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማለትም ጉምሩክ ኮሚሽን፣ ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፣ ብሔራዊ መረጃና ደኅንነት እንዲሁም ፖሊስ የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ሁሉም ወይም በተናጠል የአሠራር ግድፈት ካሳዩ የአውሮፕላን ጣቢያው ዓለም አቀፍ ስም ይጎዳል። ይህ ደግሞ ሀገር የምትመካበትን መልካም ገጽታ አጥፍቶ ጥቅሟንም፣ ክብሯንም ያሳጣታል።

ሰሞኑን የሙያ ሥነ-ምግባር በጎደላቸው የኤርፖርት ጉምሩክ ሠራተኞች ወደ አሜሪካ የምትጓዝ አንዲት መንገደኛ ላይ የተፈጸመው ተገቢ ያልሆነ ተግባር መጀመሪያ አየር መንገዱን፤ ጉዳዩ ከተሰራጨ በኋላ ደግሞ ጉምሩክ ባለሥልጣንን አስወቅሷል።

የጉምሩክ ባለሙያዋ እና የርሷ ኃላፊ የመንገደኛዋን የወርቅ ጌጥ እና የአሜሪካ ዶላሮች ይዛ መውጣት እንደማትችል አሳውቀዋት ቢሮ ውስጥ ካስገቧት በኋላ ገንዘቡን ወስደውባት ወደምትሔድበት እንደሔደች ራሷም፣ የጉምሩክ ኃላፊዎችም አሳውቀዋል።

ይህ ድርጊት አስቀድሞ በገጽታው ላይ ያጠላው አየር መንገዱን በመሆኑ በዋና ሥራ አስፈጻሚው አማካይነት አየር መንገዱን እንደማይመለከት ያሳወቀ ሲሆን የጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ በበኩላቸው ተጠርጣሪ የሆኑት ሁለት የኤርፖርት ጉምሩክ ሠራተኞች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተካሔደባቸው እንዳለ አሳውቀዋል።

ኮሚሽነሩ፤ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የተለያዩ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት አየር መንገዱ ውጤታማ እንዲሆን እና መልካም ስም እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ቀላል የማይባል ሚና እንዳላቸውም አንስተዋል። ከዚህ አኳያ እንዲህ ዓይነትም ሆነ ሌላ ሕገ-ወጥ ድርጊት ወደፊትም እንዳይፈጸም ኮሚሽኑ ጥብቅ ክትትል ከማድረግ ባሻገር በአየር መንገዱ የሚሠሩ ሠራተኞቹን በአዲስ መልክ ሊያዋቅር እንደሆነ አሳውቀዋል።

ጉምሩክ ኮሚሽን እያደረገ ባለው ጥብቅ ክትትል መሠረት በ2015 በጀት ዓመት ከደረሱት ጥቆማዎች በ83 እና በ2016 ስምንት ወራት ደግሞ በ49 ሠራተኞች እና አመራሮች ላይ ከባድ እና ቀላል አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ ተወስዷል። እርምጃው የተወሰደው ችግሮቹን ለመቅረፍ ረጅም ጊዜ የወሰደ ጥናት ከተካሔደ በኋላ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስም በመጥፎ መነሳት ለሀገር ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ጭምር ጥሩ ስላልሆነ ጉዳዩ ገንኖ ወጣ እንጂ ተመሳሳይም ሆነ ሌሎች ሕገ-ወጥ ድርጊቶች በሌሎችም የጉምሩክም ጽ/ቤቶች ሊፈጸሙ ስለሚችሉ ደንበኞች እንዲህ ዓይነት ጉዳይ ሲያጋጥማቸው በተዋረድ ለሚገኙ ኃላፊዎች ማሳወቅ አለባቸው። የጉምሩኩን አነሳን እንጂ በታክስ ጽ/ቤቶችም የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ሕገ-ወጥ ድርጊቶች ሲገጥሙም ተገልጋዮች በዝምታ ማለፍ እንደሌለባቸው እናሳስባለን።



ከቀድሞዎቹ የመ/ቤቱ ባልደረቦች በከፊል፤

# ምክር እና ዕውቀት ፍለጋ

**በሰሎሞን ወርቁ**

የገቢዎች ሚኒስቴር “ግብር ለሀገር ክብር” በሚል መርህ “ከየካቲት እስከ የካቲት” የተሰኘ ከባለፈው ዓመት የካቲት 23 ጀምሮ የግብር/የታክስ እና ጉምሩክ ሕግ ተገዥነት ንቅናቄ መድረክ አካሂዷል። የዚህ አካል ሆነ የሚኒስቴሩ እና የጉምሩክ ኮሚሽን የቀድሞ ባልደረቦች እና ሠራተኞች፣ ባለድርሻ አካላት፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን ኃላፊዎች የተሳተፉበት ውይይት መጋቢት 14/2016 ዓ.ም በስካላይት ሆቴል ተካሂዶ ነበር።

እነዚህ ተሳታፊዎች በተለያየ ደረጃ በታክስ እና በጉምሩክ ጉዳዮች ላይ ከአምስት እስከ ሰላሳ ዓመታት ያስተማሩ፣ የተመራመሩ፣ የጻፉ እና ያጠኑ ናቸው። ከዚህም በፊት በተለያዩ ደረጃዎች ተቋማቱን ያገለገሉ እንዲሁም በንግድና ዘርፍ ማህበራት እና በኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር አመራሮች ሆነው እየሠሩ ያሉም ናቸው።

ከእነዚህ ግለሰቦች ጋር መሥራት እና ልምዳቸውን መቅሰም ካላቸው የቆየ እውቀት እና ልምድ አሁንም በዘርፉ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንዲሁም በከፍተኛ የመንግስት እና የግል የትምህርት ተቋማት /ዩኒቨርስቲዎች/ ላይ በመምህርነት እና በተመራማሪነት እየሰሩ ያሉ ዶክተሮች እና ፕሮፌሰሮች ከመሆናቸው አንጻር ምክር በመለገስም ገቢዎች ሚኒስቴርን እና በጉምሩክ ኮሚሽንን አሁን ካሉበት ከፍ ወዳለ ደረጃ እንደሚያደርሱ ይታመናል።

አሁን አሁን የግብር ከፋዮች አመለካከት እየተሻሻለ፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎም እያደገ እና መንግሥትም ለሴክተሩ ያለው ትኩረት በጣም እየተሻሻለ መምጣቱ አቅም የሚፈጥር ነው። ሆኖም ግን በተለያዩ የዓለም አቀፍ መስፈርቶች ሲታይ አሁንም የመሥሪያ ቤቶቹ አፈጻጸም ጉድለት ያለበት እና ብዙ መሠራት ያለበት መሆኑን ያሳያል። በተለይ አገራችን ከምታመርተው ምርት እና ከማክሮ ኢኮኖሚው እድገት አንጻር የሚሰበሰበው ታክስ ምጥጥኑ በቂ አለመሆኑ ብቻም ሳይሆን ካለፉት ዓመታት ዝቅ ወዳለ ደረጃ እየመጣ መሆኑ ተገምግሟል። አሁንም የህብረተሰቡን አመለካከት እና ግንዛቤ ለማሳደግ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በምርምር እና ስርጸት በመጨመር የታክስ እና የጉምሩክ ወንጀሎችን በመከላከል ኢኮኖሚውን በሲስተም የተደገፈ እና በበቂ መረጃ እንዲደገፍ ማድረግ ይገባል።

ተቋማቱ ባለፉት አምስት ዓመታት በሰው ኃይል አቅም፣ በአሠራር ማሻሻያ፣ በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ እና አግልግሎትን በተቀላጠፈ እና በምቹነት በመስጠት እንዲሁም ኦንላይን በማድረግ ጭምር ትልልቅ የማሻሻያ ሥራዎችን ሠርተዋል። በዚህም የግብር ከፋዮችን የእርካታ ደረጃ ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ መጥቷል። የገቢ አሰባሰቡም በከፍተኛ ደረጃ እድገት አሳይቷል። ሌሎች ዓለማት ላይ የተፈጠሩት የታክስ አሰባሰብ ሥርዓቶች ኢትዮጵያ ውስጥም እየተፈጠሩ እና ከበፊቱ ይልቅ በአጭር ጊዜ ፈጣን አገልግሎት እየተሰጠ ነው።

የታክስ ሕጎች እና መረጃዎች ለታክስ ከፋዮች በኢሜይሎቻቸው እየተላኩ በመሆናቸው ለአሠራራቸው ቅለት ከማምጣቱም በተጨማሪ ጊዜያቸውንም ቆጥቦላቸዋል። የገቢ ሰብሳቢው ዘርፍ እና የነጋዴ ሌባና ፖሊስ ዓይነት ጨዋታን ማስቀረት የሚቻለው ቴክኖሎጂን በመታጠቅ ነው። ለዚህም ሲባል የኢታክስ ሲስተም ተግባራዊ መሆኑ ብዙ ግብር ከፋዮችን እፎይታ ሰጥቷቸዋል። የአሠራር ግድፈቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ ደግሞ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሰርኩላሮች ሲወጡ ለሠራተኞች ስልጠናዎች እየተሰጡ ሲሆን ወደፊት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በውይይቱ የገቢው ዘርፍ ከምን ተነስቶ ምን ላይ ደርሷል የሚለውን ለመለየት የአሠራር መመሪያ ፖሊሲ /Policy Roadmap/፣ የታክስ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መመሪያ /Tax Policy and Strategy guide/፣ የታክስ ሕግ ማዕቀፍ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ /Tax Law Framework Policy and Strategy/፣ መዋቅራዊ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ /Structural Policy and Strategy/ እንዲሁም የሰው ሃብት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ /Human Policy and Strategy/ ማዘጋጀት እንደሚገባም በተሳታፊዎች ተጠቁሟል።

ሠራተኞች እርካታቸው ጨምሮ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን ከፍ እንዲያደርጉ የደመወዝ እና የጥቅማጥቅም ማሻሻያዎችም ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ እተጠበቀ ይገኛል። እንዲሁም ለሠራተኞች እና ለተገልጋዮች ምቹ የሥራ አካባቢ ለመፍጠር እየተሠራ ይገኛል። የዚህ ዓመት ጥናት እንደሚያሳየው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አገልግሎት በመስጠት በኩል 87 በመቶ እና የተገልጋዮች እርካታ ደረጃው ደግሞ 83 በመቶ እንደሆነ የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ መሰረት መስቀሌ ገልጸዋል።

# እንግዳችን

አዘጋጅ:- ሺመልስ ሲሳይ

# «ግብርን በወቅቱ አሳውቆ መክፈል ከአላስፈላጊ የክርክር ሒደት ያድናል»

**- አቶ አበረ አስፋው**

**በገቢዎች ሚኒስቴር የሕግ አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ አበረ አስፋው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዳይሬክቶሬቱ አማካይነት ክርክር ስለሚያደርግባቸው ጉዳዮች፣ ስለመርታት አቅም ምንነት እና ሌሎች ተያያዥ የሕግ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሰጡንን ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል።**



**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክርክር የሚያደርግባቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?**

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክርክር የሚያደርግባቸው ጉዳዮች በግብር ይግባኝ ጉዳዮች እና በመደበኛ ፍትሐ ብሄር ጉዳዮች ላይ ነው። አብዛኛው ክርክር የሚደረገው በግብር ይግባኝ ጉዳይ ላይ ነው።

የግብር ይግባኝ ክርክር በመጀመሪያ የሚታየው በግብር ይግባኝ ኮሚሽን በኩል ሲሆን ክርክሩም በጊዜ የተገደበ ነው። የክርክር ሂደቱም ረዘመ ከተባለ በአራት ወራት ውስጥ መጠናቀቅ እንደሚኖርበት የታክስ አስተዳደር ሕጉ ይደነግጋል። መደበኛ የፍትሐ ብሔር ክርክር በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚታይ ሲሆን የክርክር ሒደቱም በፍትሐ ብሔር ሕጉ መሰረት የሚመራ በመሆኑ እንደማንኛውም የፍትሐ ብሔር ክርክር የሚታይ ጉዳይ ነው።

ግብር ከፋዮች የሚጠበቅባቸውን ግብር በራሳቸው አሳውቀው እንዲከፍሉ ይጠበቃል። በዚህም መሰረት አብዛኛው ግብር ከፋይ ታክሱን በራሱ እያሳወቀ የሚከፈል ቢሆንም በሚኒስቴሩ የስጋት መምረጫ ሥርዓት መሰረት በከፍተኛ እና መካከለኛ ስጋት በሚመደቡት ታክስ ከፋዮች ላይ በመሥሪያ ቤታችን ኦዲተሮች አማካይነት ግብሩ የሚወሰን ይሆናል። በዚህ ውሳኔ ያልተስማሙ ግብር ከፋዮች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ጽ/ቤት ቅሬታቸውን ማቅረብ ይችላሉ። በዚህም ካልረኩ ወደ ግብር ይግባኝ ኮሚሽን፤ አለፍ ካለም ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ሄደው መከራከር ይችላሉ።

**የመርታት አቅም ምን ማለት ነው? የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመርታት አቅምስ ምን ያህል ነው?**

የመርታት አቅም የምንለው ተቋማችን በሚከራከርባቸው የግብር ይግባኝ የክርክር መዝገቦች በምን ያህሉ እንዳሸነፈ በምን ያህል እንደተሸነፈ የሚገልጽ መረጃ ነው። የሚኒስቴር መ/ቤታችን የ2016 ግማሽ በጀት ዓመት የግብር ይግባኝ ክርክር የመርታት አቅም 85 በመቶ ነው። ይህ ማለት ግን 15 በመቶው ሙሉ በሙሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ ተወስኗል ማለት ሳይሆን በመዝገቦቹ ላይ በመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ተጠይቆባቸው ክርክር የሚደረግባው እና እየተደረገባቸው በመሆኑ የክርክሩን የመጨረሻ ውጤት የሚመለክት አይደለም። ሚኒስቴር መ/ቤታችን በታክስ ዙሪያ ከግብር ከፋዮች ጋር በርካታ የይግባኝ ክርክሮችን ያካሄዳል።

ነገር ግን በየትኛውም የክርክር እርከን ላይ በሚሰጡ ውሳኔዎች የተወሰኑ ማሻሻያዎች ሊደረግላቸው ይችላል። ነገር ግን በታክስ ክርክር በአብዛኛው የታክስ ክርክሮች በሂሳብ ሰነዶች ላይ ተመስርቶ የሚወሰን በመሆኑ ግብር ከፋዮች የሚኒስቴር መ/ቤቱን ታክስ ውሳኔ በተገቢው ሁኔታ የማስተባበል አቅም የላቸውም። በዚሁ አጋጣሚ ግብር ከፋዮች ወደ ክርክር ሂደት ከመግባታቸው በፊት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተወሰነው የታክስ ውሳኔ መሻሻል ወይም መታረም ያለበት ስለመሆኑ በደንብ አረጋግጠው ወደ ክርክር ቢገቡ ተመራጭ ይሆናል።

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመርታት አቅም ሲጨምር የቻለባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?**

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመርታት አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። የመጀመሪያው ምክንያት የባለሙያዎቻችን የመከራከር ብቃት በመጨመሩ ነው። ይህም ሊሆን የቻለው የባለሙያዎቻችን አቅም ለማሳደግ በየጊዜው በሚሰጡ ስልጠናዎች አማካይነት ነው። ሁለተኛው ምክንያት እኛ ክርክር የምናደርገው በቂ እና ተጨባጭ መስረጃዎችን ይዘን ሲሆን በአንጻሩ ግብር ከፋዮቻችን ወደ ክርክር የሚገቡት በቂ እና ተጨባጭ መረጃ ይዘው ሳይሆን ጊዜ ለመግዛት ብቻ በመሆኑ ነው። ይህ ድርጊት ለግብር ከፋዮችም የማይበጅ፣ ጊዜያቸውን የሚያባክን እና ላልተፈለገ ወጭ የሚዳርጋቸው በመሆኑ ከዚህ ድርጊታቸው መታቀብ ይኖርባቸዋል።



**ከ2008 በፊት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የራሱ ወንጀል መርማሪ እና የዓቃቤ ሕግ አደረጃጀት ነበረው። አሁን ግን ይህ አደረጃጀት ወደ ሌሎች መ/ቤቶች ሄዷል። ይህ በግብር አሰባሰብ ሒደቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አይኖረውም?**

ከ2008 በፊት ለበርካታ ዓመታት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የራሱ ወንጀል መርማሪ እና የዓቃቤ ሕግ ነበረው። ነገር ግን ከ2008 በኋላ በተደገረው መዋቅራዊ ለውጥ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ወንጀል መርማሪ ፖሊስ በፌዴራል ፖሊስ እንዲመራ፤ በተመሳሳይም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓቃቤ ሕግ በፍትህ ሚኒስቴር እንዲከናወን ተደርጓል። ይህም ሊሆን የቻለው የወንጀል ምርመራውም ሆነ የፍትህ ሥርዓቱ በአንድ ዕዝ መመራት ስለሚኖርበት ነው። ለታክስ ይግባኝ ጉዳይ የፌዴራል ፖሊስም ሆነ የፍትህ ሚኒስቴር ልዩ ትኩረት ሰጥተው ሥራቸውን በአግባቡ እየሠሩ ናቸው። የቀድሞው አሠራር ተለወጠ ማለት ግን የታክስ ክርክሩ ትኩረት አልተሰጠውም አይደለም።

**ግብር በወቅቱ አሳውቆ መክፈል ምን ምን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል?**

ግብርን በወቅቱ አሳውቆ መክፈል ካሉት ጠቀሜታዎች ውስጥ አንዱ ግብር ከፋዮች አላስፈላጊ ክርክር ውስጥ እንዳይገቡ የሚያደርጋቸው ነው። ግብር ከፋዮች አላስፋላጊ ክርክር ውስጥ በገቡ ቁጥር ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ ሆነው አያውቁም። ሌላው ጠቀሜታ፤ መንግሥት ከግብር ከፋዮች በሚሰበስበው ገንዘብ የተለያዩ መሰረተ-ልማቶች እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ይሠራሉ። በነዚህ መሠረተ-ልማቶች ተጠቃሚ የሚሆኑትም እራሳቸው ግብር ከፋዮች ናቸው።

**የግብር ከፋዮችን የሕግ ተገዢነት ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ምን ይጠበቃል?**

ሚኒስቴር መ/ቤታችን የሕግ ተገዢነትን በማስፈን ሃገሪቱ ከታክስ የምታገኘውን ገቢ ለማሳደግ ከበርካታ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ ይገኛል። ከነዚህ ባለድርሻ አካላት ውስጥ ዋንኛው የፍትህ ሚኒስቴር ነው። በዚህ ሚኒስቴር መ/ቤት የታክስ ጉዳይን ብቻ የሚመለከት ዳይሬክቶሬት ተቋቁሟል። ይህ ዳይሬክቶሬቱም ሥራውን በአግባቡ እያከናወነ ይገኛል።

**ተጨማሪ ሃሳብ ካለዎት?**

ግብር የሃገር ልማት መሠረት ነው። መንግሥት የተለያዩ መሰረተ-ልማቶችን ሊያሟላ የሚችለው ግብርን በአግባቡ ሲሰበሰብ ብቻ ነው። ግብር በአግባቡ ሲሰበሰብ አጠቃላይ የሃገር ዕድገት ይነቃቃል፡ መንግስትም በአግባቡ የሰበሰበውን ግብር በምላሹ ለሁሉም ዜጎች የተመቸች ሀገር የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል። ስለሆነም ግብር ከፋዮች ለዚህ ጥቅም ሲባልም ሆነ ሕጋዊ ግዴታቸውን ለመወጣት እንዲሁም ለሌላውም አርዓያ ለመሆን የሚጠበቅባቸውን ግብር በወቅቱ አሳውቀው መክፍል ይኖርባቸዋል።

ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ- ሰለሞን ወርቁ

# ደረሰኞች መያዝ የሚገባቸው ዝርዝር መረጃዎች

1. የአቅራቢው ሙሉ ስም፣ አድራሻና የተመዘገበ የንግድ ስም የታተመበት፤
2. የአቅራቢው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ቁጥር እና ለታክስ የተመዘገበበት ቀን የታተመበት፤
3. የደረሰኙ ተከታታይ ቁጥር የታተመበት፤
4. የገዥው ሙሉ ስም፣ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
5. የተገዛው፣ የተሸጠው ዕቃ ወይም የተሰጠው አገልግሎት አይነትና መጠን፤
6. ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ የሚፈለገውን የተጨማሪ እሴት ታክስ/ የተርን ኦቨር ታክስ መጠን፤
7. በፊደልና በአሃዝ የተጻፈ ጠቅላላ የሽያጭ ወይም የግብይት ዋጋ፤
8. ደረሰኙ የተሰጠበት ቀን፤
9. ደረሰኙን ያዘጋጅው እና/ወይም ገንዘቡን የተቀበለው ሠራተኛ ስም እና ፊርማ፣
10. የደረሰኝ አታሚው ድርጅት ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የታተመበት ቀን እና የአታሚው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቁጥር፤
11. ደረሰኙ እንዲታተም በሚኒስቴሩ የተፈቀደበትን ደብዳቤ ቁጥር እና ቀን ናቸው፡፡




# የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም እና ስረዛ

በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 136 ንዑስ አንቀጽ 2 ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው መመሪያ የማውጣት ስልጣን መሰረት የታክስ ከፋይ ምዝገባ እና ስረዛ አፈጻጸም በመመሪያ ቁጥር 3/2011 አውጥቷል። በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 (ሀ) የታክስ ከፋይ ምዝገባ ማለት በታክስ ህግ መሰረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሰው በጸደቀው ቅጽ መሰረት በመመዝገብ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /Tax Identification Number/ ምስክር ወረቀት መስጠት ነው። (ለ) የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማለት በታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ሰው ለታክስ ህጎች አላማ ሲባል ተለይቶ ሚታወቅበት በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ቁጥር ሲሆን የመንግስት ከፍተኛ ምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ለይቶ ለማወቅ የሚሰጠውን ቁጥር ይጨምራል።

አንድ ሰው ወይም ድርጅት ይህንን ቁጥር ለተለያ አላማ ካወጣ በኋላ ግብር የማይከፍልበት ምክንያት ተፈጥሮ የተቋረጠ ካልሆነ በቀር ሌላ ተጨማሪ ቁጥር ማውጣት አይችልም።

**የግብር ከፋይ መስያ ቁጥር መውሰድ ግዴታ ያስባቸው።-**

- በንግድ ወይም በሙያ ሥራ መቀጠርን ሳይጨምር የተሰማራ ግለሰብ ነጋዴ፤
- ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ፤
- ተቀጣሪ ሰራተኞች፤
- ገቢ የሚያስገባ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ግለሰብ፤
- የሲቪክ ማህበራት፣ የኃይማኖት ተቋማት እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፤
- የንግድ ማህበራት (ኩባንያዎች፣ የአክሲዮን ማህበራት፣ ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት፣ የሽርክና ማህበራት፣ የእሽሙር ማህበራት) እንዲሁም በንግድ ሥራ የተሰማሩ ማናቸውም ማህበራት፤
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች፤
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤
- በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት፤
- ባለልዩ መብት፤
- በጋራ ሃብትነት ያልተመዘገበ ሃብት ያላቸው ሰዎች፤
- በመንግስታት መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም በጽ/ቤት ማቋቋሚያ ስምምነት የሚቋቋሙ ድርጅቶች፤
- የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች (ተማሪዎች) ናቸው።

አንድ ድርጅት ወይም ገለሰብ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ለማውጣት እንደየገቢ አቅሙ የሚወሰን ሲሆን በንግድ ወይም በሙያ ሥራ የተሰማራ ግለሰብ ወይም አነስተኛ ግብር ከፋዮች /በከተማ አስተዳደር እና በክልሎች ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይስተናገዳሉ።

በፌዴራል ገቢዎች ደረጃ የሚስተናገዱ ግብር ከፋዮች በማህበራት ደረጃ የተደራጁ እና ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ናቸው። እነዚህ ግብር ከፋዮች የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ለማውጣት በገቢዎች ሚኒስቴር ዋናው መሥሪያ ቤት፣ በምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች፣ በምዕራብ አነስተኛ ግብር ከፋዮች፣ በሰሜን ምዕራብ አነስተኛ ግብር ከፋዮች፣ በመካከለኛ ቁጥር 1 እና በመካከለኛ ቁጥር 2 ግብር ከፋዮች እንዲሁም በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአካል በመገኘት ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች ቀድመው በመሟላት ይሆናል።

**ማህበራት (ኩባንያ፣ አክስዮን ማህበራት፣ ባለ አንድ አባል ሃላፊነቱ የተወሰነ፣ የሽርክና ማህበራት፣ የእሽሙር ማህበራት) ሲሆኑ ሲያሟላቸው የሚገባቸው መስፈርቶች፡-**

- የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ በህግ በተሰጠው አካል የፀደቀ፤
- በምስረታ ላይ ያሉ ባንኮች ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያስመዘገቡትን የንግድ ስያሜ እና አክሲዮኖችን ለህዝብ ለመሸጥ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጣቸውን ፈቃድ፤
- የቤት ኪራይ ውል የሥራው ቦታ በማህበሩ ባለቤትነት ስር ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፤
- የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ወይም የታደሰ መንጃ ፈቃድ፣ ከስድሰት ወር ወዲህ የተነሳ ፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶግራፍ እና በጣት አሻራ የተደገፈ የግል የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- አመልካቹ ወኪል ከሆነ ስለውክልናው የተሰጠውን ህጋዊ የውኪልና ማስረጃ ወይም በምስረታ ላይ ላለ ማህበር ወኪል ስለመሆኑ በሁሉም አባላት ፊርማ የተረጋገጠ በውልና ማስረጃ የፀደቀ፤
- ከማህበርተኞቹ መካከል የውጭ ሀገር ዜጋ ካለ ማንነቱን የሚገልጽ ዲጅታል መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኦሪጅናልና ፎቶ ኮፒ እንዲሁም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፀደቀ የሥራ ፈቃድ መያዝ ይጠበቅበታል።

ከላይ የተገለፁጽትን መስፈርቶች ሲያሟሉ በተቋሙ የተዘጋጀውን ቅፅ በአግባቡ በመሙላት አብረው አያይዘው ሲያቀርቡ አገልግሎቱን ወዲያው ያገኛሉ፡፡

**ከማህበራት ውጪ ያሉት ደግሞ፡-**

- የሲቪክ ማህበራት፣ የኃይማኖት ተቋማት እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ግብር መክፈል ግዴታ ባይኖርባቸውም ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ላይ ከተሰማሩ አግባብ ካለው የመንግስት አካል የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
- በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅትን በተመለከተ በውጪ ሀገር የተመሰረተበትን ድርጅት ህጋዊ ሰውነት የሚያረጋግጥ ከመንግስታዊ አካል የፀደቀ የምስክር ወረቀት፤
- በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የሚሰራበት የሥራ ቦታ አድራሻ የሚገልጽ ሰነድ፤
- የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች (ተማሪዎች)
  - በአግባቡ የተሞላ የማመልከቻ ቅጽ፣
  - የማንነት አካላዊ መረጃ መስጠት፣
  - የሚማርበት ዩኒቨርስቲ የታደሰ መታወቂያ ካርድ፣
  - ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ፣
  - መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በተመለከተ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ እና የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፤
- የመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ሲሆኑ የመ/ቤቱ ማቋቋሚያ ሕግ/አዋጅ/ እና መሥሪያ ቤቱን የሚወክለው ሰው ውክልና ደብዳቤ እና የግለሰቡ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ነው።

**ታክስ ከፋዩ የሚያሳውቃቸው ለውጦች**

አንድ ግብር ከፋይ ማሟላት የሚገባውን መስፈርቶች በመሟላት የታክስ መክፈያ መለያ ቁጥር ካወጣ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ለውጦችን ሊያደርግ ይችላል። ከንግድ አሠራር ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ለውጦችን ለማሳወቅ በወጣው መመሪያ ቁጥር 143/2011 መሰረት ማንኛውም ታክስ ከፋይ ከዚህ በታች የተመለከተውን ለውጥ ሲያደርግ ለውጡ በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

ሀ) በንግድ ድርጅቱ ስያሜ ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ለ) በድርጅቱ ስም የተመዘገበ፡-

(1) ቋሚ የንግድ ሥራ፣ የቢሮ እና የመኖሪያ አድራሻ ለውጥ፤

(2) በማምረቻ ቦታ ወይም ታክስ ከፋዩ በሚጠቀምበት መጋዘን ላይ የተደረገ የአድራሻ ለውጥ፤

(3) በፖስታ ወይም በመደበኛ እና በተንቀሳቃሽ ስልክ፤ ፋክስ ወይም ኢ-ሜይል አድራሻ ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ሐ) በዋነኛ የሥራ እንቅስቃሴው ወይም በቅርንጫፍ ወይም በንግድ ሥራው ዘርፍ ወይም መስክ ላይ የተደረገ ለውጥ፤

መ) በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የመመስረቻ ጽሁፍ ወይም የሽርክና ስምምነት ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ሠ) በአክስዮን ባለድርሻ አባላት ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ረ) በድርጅቱ ወይም በታክስ እንደራሴው የባንክ ሒሳብ ወይም የባንክ ሒሳብ ወይም የቅርንጫፍ አድራሻ ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ሰ) በታክስ እንደራሴው እና ከሚኒስቴሩ ጋር ግንኙነት በሚያደርግበት የኤሌክትሮኒክስ አድራሻ ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ሸ) በተመዘገበና በተከፈለ ካፒታል ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ቀ) የንግድ ሥራውን በከፊል ወይም በሙሉ በማቋረጥ ወይም በሽያጭ ወይም በስጦታ በማስተላለፍ ወይም በመለወጥ ወይም በዋስትና በማስያዝ በድርጅቱ ላይ የተደረጉ ለውጦች፤

በ) በንግድ ሥራ ወኪል ወይም የታክስ እንደራሴ ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ተ) የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ለካፒታል ማሳደጊያ ሲውል፤

ቸ) የገቢ ምንጭ መቋረጥ ወይም መሻሻልን በተመለከተ፡-

1) የቤት ወይም የህንጻ ወይም የመጋዘን ኪራይ ውል ሲቋረጥ ወይም ሲሻሻል፣

2) በተሽከርካሪ ወይም በኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ወይም ሌሎች የካፒታል ወይም የንግድ ሥራ ዕቃዎች የተደረገ የኪራይ ውል ሲቋረጥ ወይም ሲሻሻል፣

3) በራሱ ገቢውን የሚያሳውቅ ተቀጣሪ ሥራውን ሲለቅ ወይም ሲቀየር ወይም ደመወዝ ለውጥ ሲያደርግ፣

ኀ) ታክስ ከፋዩ ሠራተኛ ሲጨምር ወይም ሲቀንስ ወይም የሠራተኞች የደመወዝ ለውጥ ሲያደርግ፣ ለውጥን አለማሳወቅ ወይም ዘግይቶ ማሳወቅ

በመመሪያው መሰረት ለውጡን በ30 ቀናት ውስጥ ያላሳወቀ ግብር ከፋይ በታክስ አስተዳደር ዓዋጅ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል። ነገር ግን የ30 ቀን ገደቡ ካለፈ በኋላ የለውጥ ማስታወቂያ የሚያቀርብ ማንኛውም ግብር ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን 300 ብር የሚቀጣ ቢሆንም ቅጣቱ ከ20 ሺ. ብር ሊበልጥ አይችልም።

ግብር ከፋዩ ለውጡን ያላሳወቀው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ እና ማስረጃው

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በየዓይነቱ

## መጠለያ የሌላቸው ዜጎች

በቅርቡ የወጣው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም መረጃ መሠረት በዓለም ላይ 150 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ቤት አልባ ናቸው፡፡ ይህ ከዓለም ጠቅላላ ሕዝብ ሁለት በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናል፡፡

በአሜሪካ የሚገኘው የየል ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት በዓለማችን መጠለያ የሌላቸውን 20 ሀገራት ዘርዝሯል፡፡ በዚህም መሠረት፤

- ናይጀሪያ በ24 ሚሊዮን መጠለያ አልባ ዜጎቿ አንደኛ፤
- ፓኪስታን 20 ሚሊዮን መጠለያ አልባ ዜጎቿ ሁለተኛ፤
- ግብጽ 12 ሚሊዮን መጠለያ አልባ ዜጎቿ ሦስተኛ፤
- ሶሪያ 6.5 ሚሊዮን መጠለያ አልባ ዜጎቿ አራተኛ፤
- ኮንኮ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ በ5.3 ሚሊዮን መጠለያ አልባ ዜጎቿ አምስተኛ፤
- ኢትዮጵያ በ2.6 ሚሊዮን ቤት አልባ ዜጎቿ 14ኛ፤
- ቻይና በ2.5 ሚሊዮን መጠለያ አልባ ዜጎች 15ኛ ደረጃ ላይ ሲቀመጡ፤
- ኢራቅ፣ ካሜሮን እና ሆንድዩራስ ደግሞ በቅደም ተከተል 18ኛ፣ 19ኛ እና 20ኛ ደረጃዎችን ይዘዋል፡፡
- ይህን ቀመር የሠራችው ዩናይትድስቴትስ ከመቶ ሺ ነዋሪዎቿ 432ቱ ቤት አልባ ናቸው፡፡







## የጤፍ እንጀራ

በበርካታ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ወይም ኢትዮጵያውያን ባሉበት በየቀኑ ከገበታ የማይጠፋ ዋነኛ ምግብ እንጀራ ነው። ኢትዮጵያውያን እንጀራ እንደ ሱስ ሆኖብን ያለርሱ ውሎ ማደር ይከብደናል፤ እንጀራ የሌለበት ምግብ፣ ምግብ አይመስለንም።

ብዙዎች ኑሯቸው የተመሰረተበትን ሥራ "እንጀራዬ" ብለውም በመጥራት እንጀራን ተምሳሌት እስከማድረግ ደርሰናል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምግብ ሳይንስ እና ሥነ ምግብ ማዕከል ተባባሪ ፕሮፌሰር የሆኑት ዶክተር ቃለአብ ባዬ፤ ከዓመታት በፊት ጤፍን ከምግብ ሳይንስ አኳያ የሚቃኝ እና ያለውን የጤና ጥቅም በተመለከተ ባዘጋጁት ጥናታዊ ጽሑፍ፤ ‹‹ጤፍ በውስጡ ከያዘው ንጥረ-ነገር ጀምሮ እንጀራን ለማዘጋጀት እስካለው ሂደት ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት›› ብለዋል።

መጠኑ አንድ ሚሊ ሜትር ነው የሆነው አንድ የጤፍ ፍሬ ከ600 በላይ ዝርያዎች ያሉት ሲሆን በውስጡ ካርቦሃይድሬት፣ አይረን ወይም ብረት፣ ፕሮቲን፣ ከስንዴ እና ሩዝ የተሻለ ስብ (ፋቲ አሲድ)፣ ሚነራል፣ ካልሺየም፣ ፋይበር እና በርካታ ንጥረ-ነገሮችን ይዟል፡፡

### የማይፈተገው ጤፍ

በዲላ ዩኒቨርሲቲ የምግብ ሳይንስና የሥነ-ምግብ መምህሩ ዶ/ር ይሁኔ አየለ፤ ጤፍ እንደሌሎች እህሎች እንደማይፈተግ ጠቁመው እህሎችን መፈተግ የንጥረ-ነገር ይዘታቸውን ማራቆት ነው ሲሉ ይገልጹታል።

ጤፍን ወደ እንጀራ ለመቀየር የሚያልፍበት ሒደት ጠቀሜታውን ከፍ እንደሚያደርገው የሚገልጹት ዶ/ር ይሁኔ፤ የአይረን ይዘቱ የሚጨምርክት አንዱ ምክንያት የሚወቃበት መንገድ እንደሆነ ያስረዳሉ።

"ጤፍን ሜካናይዝድ ብናደርገው [በዘመናዊ የእርሻ መሳሪያ ቢመረት] ጤፍነቱ ያበቃል ወይም ከ50 ፐርሰንት በላይ አይረኑ አይገኝም። ጤፍ በከብቶች እግር ሲወቃበት ፍሬዋ ትንሽ ስለሆነች ብዙ አይረን ከመሬት ትስባለች" ያሉ ሲሆን የሚጋገርበት ምጣድ ደግሞ ሌላኛው የአይረን ምንጭ መሆኑን ተናግረዋል።

### ጤፍ ሲቦካ (Fermentation)

ከመጋገሩ በፊት እስከ ሦስት ቀናት ተቦክቶ የሚቆየው የጤፍ ዱቄት የሚያልፍበት የመብላላት (Fermentation) ሒደቱ ለጤና ተስማሚ እና ጠቃሚ እንዲሆን ያደርገዋል፤ የተወሰነውን ክፍልም ደግሞ ወደ አሲድነት ይቀይረዋል።

በመብላላቱ (Fermentation) ሂደት የሚመጣው አሲድ ለሰው ልጆች ጎጂ የሆኑ እና ለህመም የሚያጋልጡ ባክቴሪያዎችን የመራባት እድላቸውን በመቀነስ እንጀራው ጤናማና ደኅንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል። ይህም ብቻ ሳይሆን ሒደቱ ቫይታሚኖችን ይዞም ይመጣል።

### ጉርሻ ላይ ለማድቀቅ

እንደ ዶ/ር ይሁኔ ገለጻ፤ እንጀራ 'መጠቅለያ' ወይም 'ማባያ' መሆኑ አብረው የሚበሉ ምግቦች አፍ ውስጥ በሚገባ እንዲደቁ ይረዳል። ይህ ደግሞ ሥርዓተ-ምግብ በተገቢው ሁኔታ እንዲሳለጥ እና ጨጓራ ላይ ያልተገባ ሥራ እንዳይፈጠር ያግዛል።

### እንጀራ እና ጤና

### ከ—ግሉቲን" ነጻ

ስንዴን ጨምሮ የተለያዩ ምግቦች በውስጣቸው የያዙት ግሉቲን የተሰኘ ንጥረ ነገር የማይስማማቸው ሰዎች አሉ። ግሉቲን በእነዚህ ሰዎች ላይ የአንጀት ቁስለት፣ የሆድ ህመምና በአየር መሞላት፣ ድርቀት፣ ምቾት ማጣት እና መሰል የጤና እክሎችን ያስከትላል።

በተለይ በነዚህ የጤና እክሎች ለሚቸገሩት የኖርዲክ (የሰሜን ዋልታ አካባቢ ያሉ) አገራት ሰዎች ከ'ግሉቲን' ነጻ የሆነው ጤፍ ምቹ ምግብ ነው።

### ለሰውነት ጤና

"እንጀራ በፋይበር የበለጸገ ነው። ያ ደግሞ ለሆድ እቃ በጣም ትልቅ ሚና ይኖረዋል" የሚሉት ደግሞ ዶ/ር ቃለአብ ሲሆኑ ምግብ ለመመጠን እና ክብደትን ለማስተካከል እንደሚረዳ አስረድተዋል።

‹‹ባልተገባ መንገድ በፍጥነት ተፈጭቶ ወዲያው ደም ውስጥ ስለማይሰራጭ ለስኳር ታማሚዎች ጥሩ ነው ማለት ባይቻልም ከሌሎች አማራጮች አንጻር የተሻለ ሊሆን ይችላል" ብለዋል።

### የደም ማነስን ለመከላከል


‹‹ቀይ››፣ ‹‹ነጭ›› እና ‹‹ሠርገኛ›› ተብለው ቢለዩም አይነቶች ከስድስት መቶ በላይ እንደሆኑ የጠቆመው ጥናቱ ከእነዚህ የጤፍ አይነቶች በያዘው የአይረን መጠን እና የተሻለ ንጥረ-ነገሩ የሚታወቀው ቀዩ ጤፍ ነው።

### ጤፍን በሌላ ቅርጽ

ጤፍ በአብዛኛው የተለመደው በእንጀራ ወይም አልፎ አልፎ በቂጣ መልክ ተጋግሮ ቢሆንም ተጨማሪ መንገዶች እየመጡ እንደሆነ ዶ/ር ቃለአብ በጥናታቸው አመልክተዋል። በዚህም መሠረት በዳቦና በኮርን ፍሌክስ መልክም እየመጣ ነው። በተጨማሪም እርሳቸው የሚሠሩበት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጤፍ ቅይጥ የሆነ ፓስታን ለማስተዋወቅ መሞከሩን አንስተዋል። በተጨማሪም በኩኪስ እና በሌሎች የምግብ ቅርጾች እንዲሁም ከሌሎች ግብአቶች ጋር መዘጋጀት እንደሚችል አስረድተዋል።

ይህ ሁሉ ቢሆንም ጤፍ ብቻውን የተሟላ የሚባል ምግብ ስላልሆነ ከሌሎች ምግቦች ጋር አሰባጥሮ መመገብ እንደሚገባ ዶ/ር ቃለአብ ጠቁመዋል፡፡

ምንጭ፡- ቢቢሲ አማርኛ



# ሀብታሞች እንዴት ሀብታም ...

ከገጽ 1 የዞረ

አብዛኛዎቹ ሀብታሞች ምንም አይነት ቀረጥ አይከፍሉም፤ ከከፈሉም ብዙውን ጊዜ ከገቢያቸው ሦስት በመቶ ወይም ያነሰ ነው። እነዚህ ሃብታሞች በቢሊዮን የሚቆጠሩት ጥቅማጥቅሞችን በመተግበር ማደጉን ቀጥለውበታል። በሚቀጥሉት 20 ዓመታት ውስጥ አብዛኛው የዚህ ሀብት አንድ በመቶ ሀብታም በሆኑት የቤተሰብ አባላት መካከል ይንቀሳቀሳል። በአሜሪካ ብቻ ከ36 ትሪሊየን እስከ 70 ትሪሊየን ዶላር የሚገመት ሀብት ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ይተላለፋል ተብሎ ይገመታል። ይህ ትልቅ የትውልዳዊ የሀብት ሽግግር እተካሄደ እንደሆነ የበለጠ ጎልቶ ይታያል።

ሀብታሞች ይህንን የግብር ባለዕዳነት ጫና ከሚፈቱባቸው ቁልፍ መንገዶች አንዱ በጎ አድራጎት ነው። የበጎ አድራጎት አስተዋፅዖዎች የተመሰገኑ እና እንደ “መልሶ መስጠት” አይነት ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ የሚገመተው ዓለም አቀፋዊ የበጎ አድራጎት ዋጋ 2.3 ትሪሊዮን ዶላር ነው። በግምት ሁለት በመቶው ከዓለም አጠቃላይ የሀገር ምርት ውስጥ አብዛኛው ገንዘቦች በስጦታዎች የተያዙ ናቸው። ይህም እንደ ካናዳ እና ብራዚል ካሉ ሀገራት ዓመታዊ የሀገር ውስጥ ምርት መጠን ይበልጣል። ለምሳሌ፣ በአሜሪካ የበጎ አድራጎት አንዱ ገጽታ በ1976 በአሜሪካ የግብር ሕግ ላይ የወጣው አምስት በመቶ የክፍያ ደንብ ነው። በነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት ከጠቅላላ ስጦታው አምስት በመቶውን ብቻ መስጠት ይኖርበታል። ለትርፍ ያልተቋቋመበትን ሁኔታ ለማስቀጠል በየዓመቱ የገንዘብ ድጋፍ ወይም ከፕሮግራም ጋር የተያያዙ ኢንቨስትመንቶች ማቅረብ ይጠበቅበታል። በተግባራዊ ሁኔታው ይህ የአሠራር ደንብ ከግብር መክፈያው ወለል ይልቅ ስጦታዎችን ለመስጠት ጣሪያው ዝቅተኛ ይሆናል። የተቀረው 95 በመቶው የስጦታ መጠን ከቀረጥ ነፃ የሆነ የኢንቨስትመንት ገንዘብ ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው። ይህም ለአብዛኛው ባለሃብቶች መሰረቶች ስለሚሆኗቸው እድገታቸው የማያቋርጥ ሆናል።

ይህን የበለጠ ስንከፋፍልው እ.ኤ.አ. በ2020 በዓለም ላይ የስጦታዎች መሠረት አማካይ ተመላሽ መጠን 13.1 በመቶ ነበር። የ100 ሚሊዮን ዶላር ፋውንዴሽንን እንደ ምሳሌ ብንወስድ በዓመቱ ውስጥ አምስት ሚሊዮን ዶላር ብቻ መስጠት ይጠበቅበታል። ነገር ግን ስጦታው ከ113 ሚሊዮን እስከ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲቀነስ በዓመት 108 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ድርስ ይሆናል። በሚቀጥለው ዓመት ይህ የ108 ሚሊዮን ዶላር የተዘረጋ ኬክ ከ5.4 ሚሊዮን ዶላር ሲቀነስ 122 ሚሊዮን፤ በድምሩ 117 ሚሊዮን ይሆናል። ስለዚህ 100 ሚሊዮን ዶላሩ በሁለት ዓመታት ውስጥ 117 ሚሊዮን ዶላር ሆኖ ማደጉን ይቀጥላል።

እነዚህ በስጦታ ስም የሚሰበሰቡ ገንዘቦች (ይልቁንስ ታክስ ያልተከፈለ የኢንቨስትመንት ካፒታል) ወደ ካፒታሊዝም ሞተሮች ማለትም የአክሲዮን ገበያዎች፣ ቦንዶች፣ ሪል እስቴት፣ የቅሪተ-አካል ነዳጅ ኩባንያዎች፣ ወዘተ ሲዘዋወሩ ተጨማሪ የሀብት ክምችትን ያስከትላሉ።

ይህ የአምስት በመቶ ሕግ ክፍያ በአሜሪካ ውስጥ የተጀመረ ቢሆንም በዓለም ዙሪያ የበጎ አድራጎት ሞዴል መተዋወቁን ቀጥሏል። ስጦታዎችን በማሳደግ ፋውንዴሽኖች ደግሞ የሚፈለገውን አነስተኛ መጠን እየሰጡ ሀብታቸውና ኃይላቸውን በማጠናከር በትጋት የሚሠሩ ሰዎች ተንኮል በልገሳ ስም እንደቀጠለ ነው።

የዚህን ሞዴል አንድምታ ለመረዳት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ኢኮኖሚስት አያስፈልግም። ከግብር ነፃ የሆነ የበጎ አድራጎት ፈንድ የተወሰነ ክፍል ብቻ ማህበራዊ እና ስነ-ምህዳራዊ ጉዳዮችን ለመቅረፍ የሚያገለግል ነው። አብዛኛው ደግሞ በኢንቨስትመንት ገበያዎች ከፍተኛ እና ቀጣይነት ያለው ተመላሽ በሚደረግበት ጊዜ ህይወትን አጥፊ ተግባራት ላይ የሚውል ይሆናል።

### ሀብታሞች ታክስ የሚከፍሉበት ጊዜው አሁን ነው

ባደጉት አገራት በበርካታ ድርጅቶች በበጎ አድራጎት የሚለገሱ ስጦታዎች የአንድ በመቶውን የፋይናንስ ፍላጎት ለመጠበቅ የተነደፉ በመሆናቸው ግብር ሊጣልባቸው ይገባል።

በአሁኑ ጊዜ ጦርነቶች፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በዓለም ዙሪያ ያሉ ማህበረሰቦችን እየጎዱ ያሉበት ጊዜ ነው። ይህ መልካም ዕድሎችን አለመፍጠር እና የተለያዩ መልካም የአማራጭ ልዩነቶችን ማስፋት አለመቻል እና መገለል ህይወትን እየተጋፈጡ ያሉ ሰዎችን መከራ እየጨመረው ይገኛል።

ለእነዚህ ቀውሶች እንደበፊቱ ሁሉ ዓለም አቀፍ ምላሽ የሚያስፈልገው በመሆኑ የተለያዩ በጎ አድራጊዎች ልገሳቸውን ያደርጋሉ። በእርግጥም የእነዚህ ለጋሽ ድርጅቶች እ.ኤ.አ በመስከረም 2024 በተወካዮቻቸው አማካኝነት በተካሄደው ዓመታዊው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ (COP 28) የአገር መሪዎች፣ ዋና ስራ አስፈፃሚዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች እና የመንግስት ባለስልጣናት ተገናኝተው መክረዋል። እንዲሁም “መፍትሄዎችን” ለመፈለግ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ኮንፈረንስ (COP 28) ላይ መክረዋል። ብዙዎቹ በሲውዘርላንድ ዳቮስ ለሚካሄደው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም በጥር ወር በተመሳሳይ ሽፋን እንደገና ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘዋል።

ሆኖም ግን፤ በየዓመቱ የእነዚህ ክስተቶች ውጤት ምንም ለውጥ አልታየባቸውም። ምክንያቱ ደግሞ መሰረታዊ የሚባሉ ችግሮችን የሚያዩበት መንገድ እና መፍትሄዎች የሚፈልጉበት ስልት በአለም አተያይ የተገደቡ በመሆናቸው ነው። ውጤታማ ያልሆኑበት ምክንያቱም ዓላማቸው ከላይ የጠቀስነው ጉዳይ በመሆኑ እና የተዋቀሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን ለማስጠበቅ እንጂ ጥልቅ የስርዓት ለውጥ ለመፍጠር አለመፈለግ እና አለመቻል ነው።

አብዛኛው የበጎ አድራጎት ዘርፉ የስርዓት ችግር መንስኤዎችን ለመፍታት ሳይሆን የግል የገንዘብ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ የተፈጠረ ነው። ዓለም ይህንን የሚገነዘብበት ጊዜው አሁን ነው። ጉዳዩ በቶሎ እልባት እንዲያገኝ ባደረግን ቁጥር በጎ አድራጎትን ወደ አስፈላጊ እና የእውነተኛ የህብረተሰብ ለውጥ ስራ ለማምጣት ጠቃሚ መንገዶችን በፍጥነት ማግኘት እንችላለን።



### በጎ አድራጎት እንደ ዳግም ማከፋፈል

በአብዛኛዎቹ አገሮች የበጎ አድራጎት ልገሳ የሚያደርግ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ኮርፖሬሽን በተለገሰው መጠን ከገቢው ጋር ቀጥተኛ የግብር እፎይታ ያገኛል። በውጤቱም የበጎ አድራጎት ሥራ ትልቅ የግብር ቅነሳ ስትራቴጂ አስፈላጊ አካል ነው።

ዘ ኔሽን የተባለው መጽሔት በቅርቡ ባወጣው የምርመራ ዘገባ፤ ቢል ጌትስ “በጌትስ ፋውንዴሽን” እንቅስቃሴዎች በበጎ አድራጎት እርዳታ ከሰጠው በላይ በታክስ እፎይታ ያገኘው ገንዘብ የበለጠ ሊሆን እንደሚችል ገምቷል። በሌላ ምሳሌ ደግሞ በአሜሪካ ውስጥ ካሉት ትልቅ በጎ አድራጊ ለጋሾች አንዷ የሆነችው ማክኬንዚ ስኮት ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በእርዳታዎቿ መጠን፣ አይነት እና ፍጥነት የምትታወቅ ናት። ይህቺ ባለሃብት እንደ ብሉምበርግ ዘገባ ምንም እንኳን ከፍተኛ ገንዘብ ብትሰጥም ቢሊየነር ኢንዴክስ እ.ኤ.አ. በ2023 ሀብቷ ማደጉን ቀጥሏል።

ምንም እንኳን እነዚህ በጎ አድራጊዎች ከፍተኛ የግብር ጥቅማጥቅሞችን ቢያገኙም፤ እና ከስጦታዎቻቸው ውስጥ ትንሹን በእርዳታ ቢያወጡም፤ በጎ አድራጊዎች በህብረተሰባችን ውስጥ እንደ በጎ እና ልግስናን የተላበሱ እንደሆኑ የሚታሰቡ ናቸው።



የሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስልጠና ባለሙያ አቶ ዋለልኝ ጌትነት፤

# የወጪ መጋራት አከፋፈል

ከገጽ 1 የዞረ

ሥርዓቱ በሁለት መንገዶች የሚፈጽም ሲሆን እነርሱም በአገልግሎት እና በገንዘብ ናቸው።

ክፍያቸውን በአገልግሎት የሚፈጸሙት በትምህርት እና በጤና ሳይንስ ዘርፎች ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተመራቂዎች ናቸው። እነዚህ ተመራቂዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የቆዩበትን ዓመት ያህል መንግስት በመደባቸው ቦታ ማገልገል ይጠበቅባቸዋል። ይህ ማለት አንድ ተመራቂ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም አራት ዓመት ያህል የቆይታ ጊዚያት ቢኖረው በተመደበበት ቦታ አራት አመት የማገለግል ግዴታ ይኖርበታል ማለት ነው። ነገር ግን በተመደበበት ቦታ አራት ዓመት ማገልገል ሲኖርበት ለሁለት ዓመታት ብቻ ቢያገለግል የቀሩትን ሁለት ዓመታት ከነወለዱ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት በገቢዎች ሚኒስቴር የሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስልጠና ባለሙያ አቶ ዋለልኝ ጌትነት ያስረዳሉ።

በገንዘብ የሚከፈለው ክፍያ የሚመለከታቸው በመደበኛው መርሃ-ግብር በመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ከትምህርት እና ከጤና ዘርፎች ውጪ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት ሲሆኑ አከፋፈሉም በአራት መንገዶች ሊፈጸም ይችላል።

የመጀመሪያው መንገድ የቅድሚያ ክፍያ ነው። ይህ የአከፋፈል ሥርዓት ሠልጣኞች ወደ መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሲገቡ አስቀድመው ክፍያ የሚፈጽሙበት ስልት ነው። ይህ የክፍያ ሥርዓትም የ10 በመቶ ቅናሽ ይኖረዋል።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር...

ከገጽ 4 የዞረ

ተቀባይነት ካገኘ ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት እንደተወገደ የለውጥ ማስታወቂውን ማቅረብ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መቀጫው ግን ተፈጻሚ አይሆንበትም።

### የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም

የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ለታክስ ዓላማ በሚኒስቴሩ በተዘጋጀ ሰነድ ላይ ሁሉ መግለጽ ይኖርበታል። የታክስ ከፋዩ መለያ ቁጥር የተሰጠው ታክስ ከፋዩ ለታክስ ዓላማ በሚያቀርባቸው ሰነዶች ላይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን የሚገልጽ ከሆነ ሚኒስቴሩ የቀረበውን ሰነድ እውቅና ላይሰጠው ይችላል። የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው ከታክስ ወኪሉ በስተቀር ለሌላ ለማንኛውም ሰው ዋናውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ወይም መታወቂያ አሳልፎ መስጠት አይቻልም።

### የታክስ ከፋይነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

1. ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ለሁሉም ታክስ ህጎች የተጣለበት የመመዝገብ ግዴታ ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ወይም ሚኒስቴሩ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ማመልከት አለበት።
2. ምዝገባው እንዲሰረዝለት ማመልከቻ ያቀረበ ታክስ ከፋይ በሌላ ታክስ ህግ ለአንድ የተለየ ታክስ የተደረገው ምዝገባ ጭምር እንዲሰረዝለት እንዳመለከተ ተደርጎ ይወሰዳል።
3. የታክስ ከፋይነት ምዝገባ እንዲሰረዝለት ታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ሲያቀርብ ሚኒስቴሩ ለኦዲት ሊቀርብ የሚገባውን ማስረጃ በመዘርዘር በጽሁፍ በማሳወቅ ታክስ ከፋዩ ሥራውን ያቆመ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት በ30 ቀናት ውስጥ ምዝገባውን ይሰርዘዋል።
4. ሚኒስቴሩ የታክስ ከፋይነትን ምዝገባ ይሰረዝልኝ ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ ታክስ ከፋዩን የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ የመጨረሻ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል።
5. የታክስ ከፋዩ ምዝገባ የተሰረዘ ቢሆንም ሚኒስቴሩ ባከናወነው ኦዲት መሰረት ወይም ኦዲት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው እና/ወይም የታክስ ኦዲት ካላደረገ ራሱ ባሳወቀው ወይም ቀደም ብለው በተሰጡ ውሳኔዎች መሰረት የሚፈለግበትን ታክስ ዕዳ የመክፈል ግዴታ አለበት።
6. ታክስ ከፋዩ ያቀረበው ታክስ ማስታወቂያ የተጭበረበረ ወይም ከፍተኛ የቸልተኝነት ድርጊት መኖሩ በማንኛውም ጊዜ በሚደረግ ኦዲት ማረጋገጥ የተቻለ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን እንዲከፍል ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።
7. በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት ማንኛውም ሰው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ እና ይህ ሰው በታክስ ህጎች መሰረት ያለበትን ማስታወቅ ግዴታ ለሦስት ዓመታት ሳይወጣ የቀረ እንደሆነ ሥራውን ሙሉ በሙሉ በማቆሙ ምክንያት ለታክስ ህጎች አላማ መመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንዲሁም የተፈጥሮ ሰው ከሆነ መሞቱ፣ ኩባንያ ከሆነም መፍረሱ፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ህልውናው መቋረጡን ሚኒስቴሩ ሲረጋግጥ የታክስ ከፋይነት ምዝገባውን ሊሰርዝ ይችላል።
8. ከላይ የተመለከተው ቢኖርም በታክስ ከፋዩ ሞት ምክንያት የሥራው እንቅስቃሴ ካልቆመና ወራሽ ወይም ሞግዚት ተተክቶ የሚሠራ ከሆነ ህጋዊ ወራሽነቱን ወይም ሞግዚትነቱን እስከሚያረጋግጥና ስም እስኪዞር ድረስ በ12 ወር ወይም በፍርድ ቤት ንብረት አስተዳደር አስወክለው ከመጡ ጉዳዩ እስኪጠናቀቅ ድረስ የታክስ ከፋይነት የምስክር ወረቀት ላይመለስ ይችላል።
9. ሚኒስቴሩ በተጨማሪ የታክስ ምዝገባ ሊሰርዝ የሚችልባቸው ሌሎች መስፈርቶችን ሊያወጣ ይችላል።

# Tips

BY SHIMELIS SISAY

# The Tripartite agreement

The Ministry of Revenues has put forth its supreme exertion in modernizing the tax administration system since following the tax policy reforms. The digitalization effort of the ministry aimed at improving service provision, enhancing tax compliance, and collecting the revenue that is generated in the economy.

To run through this, role of stakeholders will play a pivotal role. It is known that the ministry has so many stakeholders. Among those, The Information Network Security Agency (INSA), and the Banks are the core ones.

To implement the electronic tax collection system, the Ministry has signed a memorandum of understanding with the Information Network Security Agency (INSA), Amhara Bank, and Tsehay Bank.

The memorandum was signed by Mrs. Mesret Meskele, the state minister of Revenues, Mrs. Tigist Hamid, the head of INSA, Mr. Chanyalew Demissie, the acting director of Amhara Bank, and Mr. Wossen Alemiye on behalf of Tsehay Bank.

The primary aims of the memorandum reducing tax compliance costs by improving record-keeping for tax purposes, limiting travel time and the need to visit physical tax offices, reducing administrative costs, and enhancing the efficiency of back-end data management systems and processes.

The Ministry of Revenues gives special attention to electronic tax administration facilitating service provision, enhancing tax compliance, improving tax law enforcement, and enhancing revenue collection. Implementing this technology will play a pivotal role in verifying the comparative advantage of the taxpayers.

Mrs. Meseret Meskele, the state minister of Revenues, stated that since January 30, 2016, E.c 45,212, or 93 percent of taxpayers, have announced their tax electronically, and 28,890, or 53 percent, have paid their tax electronically.

The Amhara Bank S.C. was formed according to the Ethiopian Commercial Code, adopted in 1960, Banking Sector Proclamation No. 592/2008, and NBE Directive No. 592/2008. It was officially registered with the Ministry of Trade and Regional Integration.

Since the bank started its operation, it has been committed to adapting modern technology and digital banking services to boost business efficiency, save costs, and increase accuracy.

The Amhara Bank is one of the Banks that signed the memorandum with the ministry. On his side, the central executive officer of the Amhara Bank, Mr. Chanyalew Demissie said that the Amhara Bank has more than 1.5 million customers. To deliver the service that redeemed the era the Bank is formulating its own rules, regulations, and strategies. For instance, the Bank is implementing digital Banking to give fast and efficient service to its customers.

Tsehay Bank is another bank that signed the memorandum with the ministry. The Bank was established following the Shareholders' General Assembly on February 18, 2021. The Bank's official inauguration took place on July 23, 2022, which also heralded the commencement of operations in the presence of the former Governor of the National Bank of Ethiopia; Yinager Dessie (Ph.D.).

Representative of the CEO of the Bank Mr. Wossen Alemiye said that Tsehay Bank has a vision to become one of the best private Banks in East Africa by the year 2040. To achieve this vision improving digital tax payment systems and utilizing various technologies are extremely mandatory. The Bank has more than 4,000 customers.

According to the representative, the signed memorandum has a positive impact on improving service provision, enhancing tax compliance, and collecting the revenue generated in the economy.

Finally, the Representative expressed his heartfelt gratitude for signing this historical agreement and committed to providing the best possible service to its consumers.

It was reminded the Ministry has signed the memorandum of understanding with Ethio Telecom and with the remaining Banks from 2020 to 2023.

**The Banks that signed the memorandum with the ministry from 2020 to 2023 are the following.**

| No. | Name of the Banks | Year |
|---|---|---|
| 1 | Commercial Bank of Ethiopia | June 2020 |
| 2 | Dashen Bank | June 2020 |
| 3 | Awash Bank | June 2020 |
| 4 | Berhan Bank | June 2020 |
| 5 | Abyssinia Bank | September 2020 |
| 6 | Hibret Bank | September 2020 |
| 7 | Oromia Bank | May 2021 |
| 8 | Wegagen Bank | May 2021 |
| 9 | Zemen Bank | May 2022 |
| 10 | Bunna International Bank | July 2021 |
| 11 | Debub Global Bank | July 2022 |
| 12 | Enat Bank | July 2022 |
| 13 | Anbesa International Bank | September 2021 |
| 14 | Nib International Bank | September 2021 |
| 15 | Abay Bank | September 2021 |
| 16 | Addis International Bank | October 2022 |
| 17 | Hijira Bank | January 2023 |
| 18 | Oromia Cooperative Bank | October 2022 |
| 19 | Zemzem Bank | January 2023 |
| 20 | Amhara Bank | February 2024 |
| 21 | Tesehay Bank | February 2024 |
| 22 | Ethio-telecom | January 2023 |

# የወጪ መጋራት አከፋፈል

ከገጽ 6 የዞረ

ሁለተኛው፤ ሠልጣኞች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ባሉበት ወቅት በየሴሚስተሩ የሚከፍሉበት ሥርዓት ሲሆን በዚሁም ለተጠቃሚዎቹ የአምስት በመቶ ቅናሽ ይደረግላቸዋል።

ሦስተኛው፤ በእፎይታ ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ሥርዓት ነው። ተመራቂዎቹ ሥራ ከያዙ በኋላ ለአንድ ዓመት በሚኖራቸው የእፎይታ ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ሲሆን በዚህ ወቅት ክፍያቸውን ከፈጸሙ የሦስት በመቶ ቅናሽ የሚደረግላቸው ይሆናል።

አራተኛው የአከፋፈል መንገድ የእፎይታ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከፈል ሥርዓት ነው። በዚህ የአከፋፈል ሥርዓት በቀጣሪው አማካይነት ከሠራተኛው ደመወዝ በትንሹ 10 በመቶ እየተቆረጠ ለገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ይደረጋል።

**በመመሪያ ቁጥር 154/2000 መሠረት አሠሪዎች የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡-**

- ከመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው በድርጅቱ የተቀጠሩ ሠራተኞችን የወጪ መጋራት ውል መጠየቅ፤
- የሠራተኞችን ስም ዝርዝር ለገቢዎች ሚኒስቴር ማሳወቅ፤
- የሚጠበቅባቸውን ግዴታ በየወሩ ቢያንስ 10 በመቶ ተቆራጭ በማድረግ ለገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ማድረግ፤
- መ/ቤቱን ሲለቁ ምን ያህል እንደከፈሉ እና ምን ያህል ቀሪ እንዳላባቸው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

በመመሪያ ቁጥር 71/2004 አንቀጽ 11 መሠረት አሠሪው ከላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ካልተወጣ የወጪ መጋራት ክፍያውን ከነወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት።

ይህ መመሪያ አሁንም በሥራ ላይ የሚገኝ ሲሆን ነገር ግን በአፈጻጸም ላይ ችግሮች ይስተዋላሉ። ለዚህም ችግር መከሰት የቀጣሪ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አለመወጣት አንዱ ነው። በመሆኑም ቀጣሪ ድርጅቶች በዚህ ዙሪያ ትኩረት ሰጥተው መሥራት እንዳለባቸው አቶ ዋለልኝ አሳስበዋል።



ሕግ-ግብር

አዘጋጅ፡- ሰሎሞን ወርቁ

# ያልተከፈለ ታክስ እና አስተዳደራዊ ቅጣት

**(ክፍል አንድ)**

የገንዘብ ሚኒስቴር በታክስ አስተዳደር ዓዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 136/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የአስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 09/2011ን አውጥቷል። በዚህ የአስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 09/2011 መሰረት ያልተከፈለ ታክስ ማለት "በመክፈያ ጊዜው ውስጥ ወይም በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 32 በተደነገገው መሰረት የታክስ መክፈያ ጊዜ ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ማለት ነው።" በዚህም ድንጋጌ መሰረት የፌደራል ታክስ አስተዳደር ዓዋጅ ቁጥር 983/2008 ደግሞ የታክስ መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም የሚገልጸውን በተመለከተ 1/ ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ የመክፈያ ጊዜው እንዲራዘምለት ለመ/ቤቱ የጽሑፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል። 2/ ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ መ/ቤቱ በቂ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት፡-

ሀ) ለታክስ ከፋዩ የታክስ መክፈያ ጊዜውን ሊያራዝምለት፤ ወይም

ለ) መ/ቤቱ በሚወስነው መሠረት ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ሊያደርገው ይችላል።

3/ መ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለቀረበው ማመልከቻ የሰጠውን ውሳኔ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጠዋል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) መሠረት ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ የአንድን ጊዜ ክፍያ ካልከፈለ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ባቆመበት ጊዜ ያለውን ቀሪ ክፍያ በሙሉ እንዲከፍል መ/ቤቱ ወዲያውኑ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

5/ የታክስ መክፈያ ጊዜው እንዲራዘም ወይም ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በዘገየው ክፍያ ላይ ከመጀመሪያ የታክስ መክፈያ ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ የመክፈል ግዴታውን እንደማያስቀር ይደነግጋል።

**ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶችን በተመለከተ**

በመመሪያ ቁጥር 09/2011 ክፍል ሁለት አንቀጽ 4 መሰረት ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶችን በተመለከተ

1. ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር በተያያዙ ቅጣቶች ተፈጻሚ የሚሆኑት በሕግ የመመዝገብ ግዴታ ላለባቸው እንዲሁም ሥራቸውን ሲያቆሙ ምዝገባው እንዲሰረዝ የማድረግ ግዴታ ለተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ነው።
2. በአዋጁ አንቀጽ 101/4/ መሠረት ማንኛውም ሰው ያለ በቂ ምክንያት ምዝገባ እንዲሰረዝለት ያላመለከተ እንደሆነ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ማመልከት ከነበረበት ቀን ጀምሮ ምዝገባው እንዲሰረዝ እስካመለከተበት ቀን ወይም በመ/ቤቱ አነሳሽነት ምዝገባው እስከተሠረዘበት ቀን ድረስ ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነ ጊዜ አንድ ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል።

የአፈጻጸም በቂ ምክንያት ማለት ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፍልበት የንግድ ሥራ ካቆመ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎች ያጋጠሙ፣ ታክስ ከፋዩ ወይም የታክስ እንደራሴ በጽኑ ህመም ላይ የሚገኙ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ እንደሆነ ነው። ለአዋጁ አፈጻጸም በቂ ምክንያት ማለትም ታክስ ከፋዩ ታክስ የማይከፍልበትን የንግድ ሥራ ካቆመ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎች ያጋጠመው እንደሆነ ታክስ ከፋዩ ወይም ታክስ እንደራሴው በጽኑ ህመም ላይ የሚገኙ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ እንደሆነ ነው።

**ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት**

መመሪያ ቁጥር 09/2011 ክፍል ሁለት አንቀጽ 5 ላይ የአዋጁን አንቀጽ 102 መሰረት በማድረግ ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት ዘርዝሯል።

በዚህም መሰረት በመመሪያ ቁጥር 09/2011 ክፍል ሁለት አንቀጽ 5 ላይ፡-

1/ ለአዋጁ አንቀጽ 102 አፈጻጸም በታክስ ሕጉ መሰረት መያዝ የነበረበት ሰነድ ማለት

ሀ) የገቢ ግብርን በሚመለከት ለደረጃ ሀ የትርፍ እና ኪሳራ እንዲሁም የሀብት እና እዳ መግለጫ፤ ለደረጃ «ለ» የትርፍ ኪሳራ መግለጫ እንዲሁም እነዚህን መግለጫዎች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑ ሰነዶች፤

ለ) የተጨማሪ ዕሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ የሚመለከት የግዥ እና ሽያጭ መዝገብ እና ታክሱን ለማስላት የሚረዱ ደጋፊ ሰነዶች፤

ሐ) የኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት ታክሱን ለማስላት የሚያግዙ የሒሳብ መዛግብት እና ደጋፊ ሰነዶች፤

2. የታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንደያዘ የሚቆጠረው ያቀረበው ሰነድ ስለመዝገብ አያያዝ መስሪያ ቤቱ በሚያመጠው መመሪያ መሰረት የቀረበ እና አስፈላጊ ደጋፊ ሰነዶች እንዲቀርብ መስሪያ ቤቱ ሲጠይቀው ያቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው።

3. ለአዋጁ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) እና (ለ) አፈጻጸም የታክስ ዘመን ማለት፡-

ሀ) ለገቢ ግብር ማስታወቂ የሚቀርብበት ታክስ የሚሸፍነው የአንድ ዓመት ጊዜ፤

ለ) ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ እንደታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን አንድ ወር ወይም ሦስት ወር፤

ሐ) ለተርን ኦቨር ታክስ የደረጃ ሀ ግብር ከፋዮች እንደ ታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን አንድ ወር ወይም ሦስት ወር፣ ለደረጃ ለ ታክስ ከፋዮች ሦስት ወር ነው፤

መ) ለኤክሳይዝ ታክስ ምርት አንድ ወር ነው።

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 102 መሰረት ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣትን እንደሚከተለው ዘርዝሯል፡-

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በታክስ ሕግ መሠረት መያዝ የሚጠበቅበትን ማንኛውንም ሰነድ ያልያዘ ታክስ ከፋይ በታክስ ሕጉ መሠረት ሰነዱ መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል ያለበትን ታክስ ሃያ በመቶ ቅጣት ይከፍላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሰነድ መያዝ ሲኖርበት ያልያዘ ታክስ ከፋይ ሰነዱን መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል የሚኖርበት ታክስ የሌለ እንደሆነ፡-

ሀ) ለገቢ ግብር ሲሆን ታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት ለእያንዳንዱ የታክስ ዘመን ሃያ ሺ ብር፤

ለ) ለሌላ ማንኛውም ታክስ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት የታክስ ዘመን ሁለት ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል።

ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣትን በተመለከተ

በአዋጁ አንቀጽ 103 /3/ አፈጻጸም "የገንዘብ ጥቅም" ማለት ታክስ ከፋዩ ወይም ሌላ ሰው የራሱ ልሆነውን መለያ ቁጥር በመጠቀም በሠራው ሥራ ካገኘው ሽያጭ ገቢ፤ ገቢውን ለማግኘት ያውጣው ወጪ ከቀነሰ በኋላ ያለው ልዩነት ነው። በአዋጁ አንቀጽ 103 /3 ላይ "ታክስ ከፋዩ ወይም ሌላ ሰው ያገኘው የገንዘብ ጥቅም ከአስር ሺ ብር የሚበልጥ ከሆነ የሚከፍለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ካገኘው ጥቅም ጋር እኩል ይሆናል።" በማለት ተቀምጧል።

**የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚስከትለው ቅጣት**

1/ የታክስ ማስታወቂያን ዘግይቶ በማቅረብ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 2/35 መሰረት የታክስ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው በሚገባ የተባሉት እንደሚከተለው በዝርዝር ተቀምጠዋል።

ሀ) በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 መሰረት በሚኖርበት የታክስ ማስታወቂያ፤

ለ) በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 መሰረት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዘውን ታክስ በሚመለከት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፤

ሐ) በተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ መሰረት የሚቀርብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ፤

መ) ወደ አገር ውስጥ በገባ ዕቃ ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ወይም ኤክሳዝ ታክስ የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፤

ሠ) በኤክሳይስ ታክስ አዋጅ መሰረት በሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፤

ረ) በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሰረት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ እና

ሰ) በአዋጁ መሰረት በታክስ ከፋዩ መቅረብ የሚኖርበት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ነው።

2/ በአዋጁ አንቀጽ 104 (1) ለተጣለው ቅጣት "የታክስ ጊዜ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(38) በተሰጠው ትርጉም መሰረት ሆኖ የቅጣቱ አወሳሰን፡-

ሀ) ለገቢ ግብር አዋጅ በዓመት፣

ለ) ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ እንደታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን በየወሩ ወይም በየሦስት ወሩ፣

ሐ) የደረጃ "ሀ" የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ እንደ ታክስ ከፋዩ የግብይት መጠን ለእያንዳንዱ በወር ወይም በሦስት ወር፣

መ) ለኤክሳዝ ታክስ በወር፣

ሠ) ለደረጃ "ለ" ለተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች በየሦስት ወሩ፣

ረ) ከተከፋይ ሒሳብ ተቀንሶ የተከፈለን ሳይጨምር የሰንጠረዥ መ ገቢ በአዋጁ አንቀጽ 104 መሰረት የሚሰላ ይሆናል።

3/ በአዋጁ አንቀጽ 104 ማለትም "የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት"ን በተመለከተ፡-

1/ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ ያልተከፈለውን ታክስ አምስት በመቶ፤ ሃያ አምስት በመቶ እስኪሞላ ድረስ ቅጣት ይከፍላል።

2/ ለመጀመሪያው የሂሣብ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚከፍለው ቅጣት ከሃምሳ ሺ ብር አይበልጥም።

3/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ያልተከፈለ ታክስ ነው" የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክሱ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው።

4/ በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው ቅጣት አስር ሺ ብር እና በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን መቶ በመቶ ያነሰ አይሆንም፡-

5/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው ሊከፍል የሚገባው ታክስ የሌለ እንደሆነ፣ የታክስ ማስታወቂያ ሳያቀርብ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ አሥር ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል። የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው የዘገየው የታክስ ማስታወቂያ እንደ አንድ ጥፋት ተቆጥሮ አንድ ቅጣት ተግባራዊ በማድረግ ነው። ይህ አንቀጽ በደረጃ "ሐ" ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

**(ይቀጥላል)**




**የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ**

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

**እሴቶች**

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)